# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 41 የካቲት 19 2001 ዓ.ም

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ግዜ

## ወያኔ የምትታለብ ጥገት ያላትን የተሌኮሚኒኬሽን መስሪያ ቤት ጡት ይዞ አለቅ ብሏል።

የመለስ ባለቤት ጭምር እንደላሜ ቦራ የምታልበው የቴሌኮሚንኬሽን መስሪያ ቤትን ወደግል ይዞታ የማዛወሩ ሃሳብ ፈጽሞ የማይታሰብ ነው ሲሉ የወያኔ የንግድ ሚንስቴር ግርማ ብሩና የመለስ የኢኮኖሚ አማካሪ ንዋይ ግብረአብ አስታወቁ።

ሁለቱ የመለስ ባለሚሎች ይህንን ያስታወቁት ኢትዮጵያ የአለም ንግድ ድርጅት አባል ለመሆን ባቀረበችው ማመልከቻ መሰረት ሚሟላት ካለባት ቅድመ ሁኔታዎች ከፍሉ በመንግሥት ጥብቅ ቁጥጥርና ይዞታ ሥር ያሚገኙትን እንደ ባንክ፤ መብራት ሃይልና ቴሌኮሚኒኬሽን የመሳሰሉትን ተቋማት ለግል ኢንቨስትመንት ክፍት የማድረግ ሃላፊነት እንደሚኖርባት ለተጣለባት ግዴታ አገዛዙን ወክለው በሰጡት መግለጫ ነው።

ይህ በግርማ ብሩና በመለስ አማካሪ ንዋይ ግብረአብ በኩል የተሰጠውን የወያኔ አቋም የገመገመው የብሉም በርግ ጋዜጠኛ የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት ከመንግሥት ይዞታና ቁጥጥር ውጭ በሆኑባቸው ጎረቤት ኬንያና ደቡብ አፍሪካ ካለው የአገልግሎት ዋጋ ክፍያ ጋር ሲያነፃጽር የወያኔ ቅምጥሎች እንዳሻቸው የሚፈነጩበትን ሃብት ለማግበስበስ ሲባል በአገራችን የሚከፈለው የአገልግሎት ዋጋ በየትም የአለም ክፍል የሌለ እንደሆነ ዘግቦአል። በዚህም መሰረት ፍጥነት ያለው የኢንተርኔት መስመር ዋጋ በኢትዮጵያ ሁለት ሺህ ዶላር በወር የሚያስከፍል ሲሆን በደብቡ አፍሪካ ግን ከ60 አስከ 59 የአሜሪካ ዶላር ፣ የሞባይል አገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችለውን ሲም ካርድ ለማግኘት በአገራችን የሚጠየቀው 35 የአሜሪካን ዶላር በኬንያና መንግስት አልባ በሆነችው ሶማሊያ ጭምር ከ2 አስከ 5 ዶላር ብቻ እንደሆነ አስታውቆአል።

በቴሌኮሚኒኬሽን የሚሰሩ አንድ የስራ ሀላፊ ለአዲስ አበባ ዘጋቢያችን እንደገለጹት ወያኔ ህብረተሰቡን የእጥፍ እጥፍ ማስከፈሉ ሳያንስ የመስሪያ ቤቱን ገቢ ጥርግ አድርጎ መውሰዱ አንጀት እንደሚያቃጥል ተናግረዋል። “መስሪያ ቤታችን ያለበት ጫና ተነግሮ የሚያልቅ አይደለም።አዜብ መስፍን በግድ ፎቄን ካልተከራያችሁት ብላ የአስር አመት ስልሳ ሚሊዮን ብር አስከፈለችን።እንደ ዜድ ቲ ካለ ምንም የስራ ችሎታ የሌለውን ካማፓኒ የሚሊዮን ዶላሮች ስራ ካለምንም ጨረታ ይሰጠዋል።ኩባንያው ደግሞ በባለስልጣናቱ ዘመድ ስም በውጪ ሀገር በተከፈተ የባንክ ደብተር ዶላሩን ያካፍላል።በመሀል የኢትዮጵያ ህዝብ ይጎዳል” ብለዋል።

እንደ ሴልቴል አይነት ከሀያ ባላነሱ የአፍሪካ ሀገራት በርካሽ ዋጋ የሞባይል አገልግሎት የሚያደርሱ ዘመናዊ እና ግዙፍ የቴሌኮም ድርጅቶች ኢትዮጵያ ለመግባት እና ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ለማዳረስ ከፍተኛ ፍላጎት ቢያሳዩም በወያኔ መከልከላቸው ይታወቃል።እንደ ስራ ሀላፊው እንደ ሴልቴሌ ያሉ ድርጅቶች ከመቶ ሚሊዮን ዶላር በላይ ከፍለን በሀገሪቱ ገበያ እንግባ እያሉ ሲለምኑ ወያኔ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ዶላር ከፍሎአቸው ወደ አገር ያስገባው ዜድ ቲ የተባለው ካምፓኒ የፈየደው ነገር እንደሌለ የአደባባይ ሚስጥር ሆኖአል ብለዋል።

ኢትዮጵያ የስልክ አገልጎሎትን በማስገባት እና በማስተዋወቅ በአፍሪካ ቀዳሚ ብትሆንም በወያኔ ጎታች እና ሙሰኛ ፓሊስ የተነሳ በአሁኑ ጊዜ አነስተኛ የሞባይል ተጠቃሚ ያለባት ሀገር ለመሆን መብቃቷ ይታወቃል።

ካሱ ይላላ በአንድ ወቅት የቴሌኮሚኬሽን ካለበት ከፍተኛ የሙስና ችግር ተላቆ ለህብረተሰቡ የተቀላጠፈ አገልግሎት ሊሰጥ የሚችለው ወደ ግል ይዞታ ቢዛወር ነው ለሚለው አስተያየት «ቴሌን እንዴት እንሸጣለን።ቴሌ እኮ የምትታለም ጥገት ላም ናት” ማለቱ አይዘነጋም።

## የኦጋዴን ግጭት እየተባባሰ በመሄድ ላይ ነው።

### የኦጋዴን ነጻ አውጭ ግንባር 140 የወያኔ ወታደሮችንና ጀሌዎቻቸውን ገዲያለሁ የደገሃቡር አካባቢንም ተቆጣጠሪያለሁ ሲል አስታወቀ::

የኦጋዴን ነጻ አውጭ ግንባር ከትናንት በስቲያ ይፋ በአደርገው መግለጫ ከ140 በላይ የሚሆኑ የወያኔ ወታደሮችንና በሚሊሺያነት የራሳቸውን ህዝብ መልሰው ለመውጋት የተሰለፉትን መደምሰሱን አስታውቆአል። እንደ ግንባሩ መግለጫ 29 የግንባሩ ተዋጊዎችም በውጊያው ላይ መሰዋታቸው ተያይዞ ይፋ ሆኖአል። በተሸነፈበት ግንባር ሁሉ አሸናፊነቱን የሚወሽከተው የመለስ አገዛዝ ቃል አቀባይ በተለመደው ቅጥፈት ውግያው የተደረገ በአማጽያኑና እራሱን ከአማጽያኑ ጥቃት በሚከላከለው የአካባቢው ህዝብ መሃል እንደሆነ ከመግለጽ ያለፈ የሰጠው ዝርዝር የሟቹች ቁጠር የለም።

ይህ በእንዲህ እንዳለ
ወያኔ በውርደትእና በአሰቃቂ ሽንፈት ከሶማሊያ ከወጣ ከሳምንታት በሃላ ተመልሶ እየገባ እንደሆነ አልጀዚራ የሚባለው የዜና አውታር ዘገበ።አልጀዚራ ከሶማሊያ ድንበር ጥቂት ኪሎሜትሮች ገባ ብላ የምትገኘውን የካላቤርካ ከተማ ነዋሪዎችን ጠቅሶ እንደዘገበው የወያኔ ወታደሮች በታንክ ታጅበው ሰኞ እለት በከተማዋ መግባታቸውን እና በነጋዴዎች ላይ ኬላ አበጅተው ቀረጥ በመሰብሰብ ላይ እንደሆኑ ዘግቧል።

ልማደኛው በረከት ስምኦን ዘገባውን ቢያስተባብልም የእስላማዊ ፍርድ ቤቶች ህብረት ተወካይ ሼክ አብዱርሀማን ኢብራሂም ለአልጀዚራ በስልክ በሰጡት ቃለምልልስ<<የወያኔን ዳግም ወረራ አንቀበለውም።ከድንበራችን በሃያ አራት ሰአት ውስጥ ካልወጣ ጦርነት እናውጅበታለን>> ብለዋል።

የወያኔ እንቅስቃሴ በደም ነፍስ የሚመራ እና ዉሉ የጠፋበት ነው ያሉት ታዛቢዎች ከቀናት በፊት ከሶማሊያ ለወጣው ሰራዊቱ ሽልማት ሰጥቻለሁ ያለ አገዛዝ ተመልሶ ሶማሊያ መግባቱ አስገራሚ ነው ብለዋል።ታዛቢዎቹ ሲቀጥሉ በወያኔ መላቅጡ በጠፋበት ፓሊሲ እና መረን በለቀቀ ሙስና 12 ሚሊዮን ኢትዮጵያዊያን በችጋር እየተጠበሱ ከሞት ጋር ትንንቅ በሚያደርጉበት በዚች የጭንቅ እና የመከራ ሰአት ዘረኛው አምባገንን መለስ ሀገሪቱን ወደ ዳግም የውክልና ጦርነት መክተቱ ፍጹም ሞራለቢስነት እና አውሬነት ነው ብለዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ወያኔ ሙሽታሂል በተባለች በሶማሌ ክልል በምትገኝ አነስተኛ ከተማ በርካታ መኪናዎችን ማገቱን የግንቦት 7 ምንጮች አመለከቱ።እንደ ምንጮችችን ዘገባ የተለያዩ የመገልገያ እና ምግብ የጫኑ መኪናዎች ወደ ዋርዴር ሲጓዙ ነው የታገቱት። በባለፉት ሳምንታት በርካታ የወያኔ ወታደሮች በሶማሊያ እና በኢትዮጵያ ድንበር ላይ የታዩ ሲሆን ለሶማሌ ክልል ህዝብ እቃ እና ምግብ የጫኑ መኪናዎችን ማገድ መቀጠላቸው ተገልጿል።እንደምንጮቻችን ገለጻ ከዚህ ቀደም በተመሳሳይ ወያኔ የጭነት መኪናዎችን እያገደ ወታደር እና የጦር መሳሪያ ወደ ውጊያ ቀጠና እንደሚያመላልስበት ገልጸዋል።

## ማስታወቂያ

### ለአንድነት፣ ለፍትህ፣ ለሰብአዊ መብት እና ለሐገር ህልውና የተጠራ ሕዝባዊ ሰልፍ!

በሃገራችን ወያኔ/ኢህአዴግ በሕዝብ ላይ እያደረሰ ያለውን ከፍተኛ የመብት እረገጣ፣ አፈና እና ሐገር መሸጥ፣ ለመቃወም እና በግፍ በእስር እየማቀቁ ያሉትን እንዲፈቱ የሚጠይቅ አለም አቀፍ ሰልፍ በሚቀጥለው ሳምንት ይደረጋል፡፡

(ዝርዝሩ ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

# በ2002 ፍትሃዊና ርቱዕ ምርጫ እንዴት?

በአንድ አመት ከሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ኢትዮጵያውያን እንደገና ወደ ምርጫ ጣቢያዎች እንዲሄዱ ሊጠየቁ ነው። የገዢው ቡድን "በደሜ ያገኘሁትን ስልጣን በአፋቸው ጤፍ ለሚቆሉ ምሁራን አላስረክብም" ማለቱን የግንቦት 97 ምርጫም ብቻ ሳይሆን፣ ባለፈው አመት ባካሄደው "የብልግና ምርጫ"ም ግልፅ አድርጎታል ። በዚህ የወያኔ ባህርይና አድራጎት ላይ በመመስረት፣ የግንቦት ሰባት ንቅናቄ፣ ይህ ፀረ-ዴሞክራቲክ ስርአት አስቀድሞ ካልተወገደ፣ ፍትሃዊና ርቱዕ ምርጫ ማካሄድ የማይታሰብ ነው የሚል አቋም ከፅንሱ ጀምሮ የቆመበት ዕምነት ነው። ንቅናቄያአችን ተመስርቶ በተንቀሳቀሰባቸው ባለፉት 9 ወራትም ቢሆን፣ የስርአቱ ፀረ-ህዝብ ባህርይ ይበልጥ እየተጠናከረ ሄደ እንጂ ምንም መሻሻል አላሳየም። በዚህ ሁኔታ የ2002 ምርጫ እንዴት ሊካሄድ ይሆን? በሰላማዊ መንገድ ታግለን ለውጥ እናመጣለን የሚሉ ሃይሎችስ እንዴት ነው ካሰቡት መድረስ የሚችሉት?

ምርጫ የሚካሄደው እንደው ዝም ብሎ የምእራብ መፅዋቾች ያስፈልጋል ስላሉ ለይስሙለ ሳይሆን፣ ነጋድራስ ገብረህይወት ባይከዳኝ እንዳሉት፣ ጠንካራ መንግስት ከህዝብ ልብ ስለሚቀዳ ነው ። አዎን ከህዝብ ልብ የተቀዳ መንግስት የሰላምና መረጋጋት ምንጭ ነው። ቁልፍ ለሆነው የስልጣን ሽግግር ጉዳይ መፍትሄ ስለሚያስገኝለት፣ ዜጎች ወደሌሎች አጣዳፊ ወደሆኑ ሃገራዊ ጉዳዮች የተባበረ አቅማቸውን ለማዋል ቦይ የሚቀድ፣ ጎዳና የሚጠርግ ነው። ኢትዮጵያችን ከገጠሙዋት የኢኮኖሚ ድቀት፣ የብሄረሰቦች ግጭት፣ የጤናና ትምህርት እጦት አኳያ ሲመዘን፣ ከህዝብ ልብ የተቀዳ መንግስት ቅንጦት ሳይሆን፣ ለሃገሪቱ ቀጣይነት መተኪያ የሌለው መሳሪያ ነው ብሎ ንቅናቄያችን ያምናል። ምርጫም መካሄድ ያለበት የስልጣን ሽግግርን ጉዳይ እልባት አስገኝቶልን፣ ሀገራችን መላ አቅሟን ወደልማት ለማዋል እንድትችል ስለሚያደርጋት ጭምር ነው።

ፍትሃዊና ርቱዕ ምርጫ ለማካሄድ ደግሞ፣ የጨዋታ ህጉ ግልፅ፣ ዳኞቹ ከወገንተኝነት የፀዱ፣ የመከላከያና የፀጥታ ሃይሉ ከገዢው ፓርቲ የተለዩና ለህግ-መንግስታዊ ስርአት የቆሙ፣ የመገናኛ ብዙሃን ሁሉንም ወገኖች በእኩል የሚያስተናግዱ ሊሆን ይገባል። በወያኔ ክርን ስር የምትደቀው ሃገራችን ኢትዮጵያ ከነዚህ ከተጠቀሱት መለኪያዎች ውስጥ አንዱን እንኳ አታሟላም ።ወያኔ ዛሬም ቢሆን በህዝብ አደባባይ፣ በግልፅ ተወዳድሬ በህዝብ ድምፅ ለመዳኘት፣ ህዝብ ድጋፉን ከነፈገኝም ለመሸነፍ ፈቃደኛና ዝግጁ ነኝ ብሎ ተናግሮ አያውቅም። ምርጫውንም በበላይነት እንዲመራ ሃላፊነት የተሰጠውን የምርጫ ቦርድ ገለልተኝነት ሊያረጋግጥልን ፈፅሞ ፈቃደኛ አልሆነም። ይባስ ብሎም በራሱ ጀሌዎች ሰግስጎታል። ፀጥታውና መከላከያ ሃይሉም ለኢትዮጵያ ህገ-መንግስት ሳይሆን፣ የወያኔ የፖለቲካ አጀንዳ ለሆነው "አብዮታዊ ዴሞክራሲ" ወገንተኛ መሆናቸውን ጠዋት ማታ ሲደሰኩር የምንሰማው ነው። በመገናኛ ብዙሃን ላይ የተጣለውን እገዳ አለም የሚያውቀው ጉዳይ ነው። የተቀናቃኝ ፓርቲ መሪዎችም፣ በዘፈቀደ ወህኒ እየተወረወሩ ነው። በዚህ አስከፊ ሁኔታ እንዴት ተደርጎ ነው፣ ትርጉም ያለው ምርጫ ማካሄድ የሚቻለው?

የግንቦት ሰባት ንቅናቄ፣ ወያኔ ከስልጣን ሳይወገድ ፍትሃዊና ርቱእ ምርጫ ማድረግ እንደማይቻል፣ ከ18 አመታቱ ልምድ በተጨማሪ የግንቦት 97 ምርጫ ልምድ ያረጋገጠው መሆኑን ቢያምንም፣ ወያኔን በሰላማዊ መንገድ ለመለወጥ እንችላለን የሚሉ ሃይሎችን ለመኮነን ፈቃደኛ አይደለም። ሆኖም፣ የይድረስ ይድረስና በተናጠል የወያኔ ምርጫ ውስጥ እንዳይገቡና፣ ፍትሃዊና ርቱዕ ምርጫ ለማድረግ ካሁኑ መሟላት ስለሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች ለራሳቸው አባላት፣ ለኢትዮጵያ ህዝብና ለአለም ህብረተሰብ፣ በግልፅ ማቅረብና፣ ለነዚህም ሁኔታዎች መሟላት ተገቢውን ሰላማዊ ትግል ማጧጧፍ ይጠበቅባቸዋል እንላለን።

## ውድ አንባቢዎቻችን

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን።

**g7radio@ginbot7.org**

## የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ

የሥርጭት ሞገድ ለውጥ አድርጓል።

በዚሁ መሰረት ከአሁን ቦኋላ በ7485 KHZ በ41 ሜትር ባንድ እና በ9610 KHZ በ 31 ሜትር ባንድ ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

# አስተያየትና ምላሽ

## መልእክት፡ ከእውነተኛ የህወሃት አባላት።

### ለግንቦት 7 ጋዜጠኞች

ራዲዮናችሁን እናዳምጣለን፣ ጋዜጣውንም እናነባለን። ባለንበት ቦታ ሁሉምን የምናደርገው ተደብቅን ነው። አማርኛ መጻፉ ቸግሮናል። መቼም ወያኔዎች ናቸው ብላችሁ አናነብም በራዴዮ፣ በጋዜጣም አናትምም እንደማትሉን ተስፋ አለን። ለምርጫ 97 ዶ/ር ብርሃኑ አዲግራት መጥተው አነጋግረውን ነበር። እኛ በትግርኛ ስንጠይቃቸው እርሳቸው በአማርኛ ነበር የሚመልሱት። በአዲግራት ከተማ ህዝብ ደስታው ምን እንደሚመስል ዶ/ር ብርሃኑ በአይን አይተዋል። ፊርማ ፈርሙልኝ እያለ ያስቸገራቸውን የወጣት ብዛት እራሳቸው ያውቁታል። ከዛ ቀን በኋላ በአዲግራት ደስታ አልታየም። ዘረኛ ለሚሉን በጭፍን ደጋፊ ለሚሉን በዛ ቀን ስብሳባ ውሸት መሆኑን አሳይተናል። ይህንን የምንለው ለወያኔዎች ቦታ የለንም ብላችሁ የላክልናችሁን ቁሻሻ መጣያ እንዳትጥሉት በመፍራት ነው። ዶ/ርን ጠይቁ እኛ ምን አይነት ሰዎች እንደሆንን ይነግሯችኋል። ካመናችሁበት የተበላሸ አማርኛውንም አስተካክሉን። እኛ እውነተኛዎቹ የህወሃት ታጋዮች የህወሃት ምስረታ በአል ለማክበር አቶ መለስ ድግስ በሚደግሱበት እለት እኛ ምን እንደሚሰማን ህዝብ ይወቅልን። ይህን በራዴዮ ከሰማነውና በጋዜጣው ካየነው ሌላም ብዙ ነገር እናደርሳችኋለን በርቱ። እኛም እንበረታለን።

### ህወሃትነት ከነመለስ ስልጣን በላይ ነው!!።

ላለፉት ሁለት አመታት አቶ መለስ ወደ ሜዲያ ብዙም ብቅ አይሉም ነበር። ብቅ ካሉም ወሬያቸው በጉልበት የያዙትን የጠቅላይ ሚንስትርነት ሀላፊነት መልቀቅ እንደሚፈልጉ፣ ግን እንዳይለቁ እየተለመኑ እንደሆነ መናገር ነው።

በመጀመርያ የሚለምናቸው ማነው? እኛ እውነተኛ ታጋዮች (ህወሃቶች) እንደሁ፣ አይደለም ለኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚንስትርነት የፓርቲውንም ስልጣን በጉልበታቸው ነጥቀውን ነውና የያዙት ለቦታውም ስለማይመጥኑ እሱንም ጨምረው አሁኑኑ እንዲለቁ ነው የምንጠይቀው።

ከዳተኛ፣ አገር ከጂ፣ አጭበርባሪና ነብሰገዳይና የሰው ትግል ቀማ መሆናቸውን ካወቅን ብዙ አመታትን አስቆጥረናል። ይህ ትግል ብዙ የሚገርም መስዋትነት ተከፍሎበታል። እሳቸውንና ስብስባቸውን ስልጣን ላይ ለማውጣትና እንዲጨማለቁበት አልነበረም። እለቃለሁ አልለቅም መመጻደቁን ይተውት። ትግሉን ከታለመበት አላማ፣ መሰዋትነት ከተከፈለበት ግብ ውጪ እንዲሄድ ያደረጉት እኛን በግምገማ ጠፍረው ይዘውን ነው። የተቃወሟቸውን ለድርጅቱ ለአገርም ለህዝብም ለእውነትም የቆሙትን፣ ደፍረው የተከራከሯቸው ጓዶቻችን ምን እንደደረሰባቸው እናውቃለን። በህይወት ካሉት ስንቶች በእስር በምን አይነት የኑሮ ሁኔታ እንዳሉ የምናውቀው ነው። በየመንገዱ በሰበሰቧቸው የድል አጥቢያ አርበኞችና በተወሰኑ የርሳቸው ቤጤ ከዳተኞች እየመላለሱ እንዲመርጡት አድርጎ የያዘውን የድርጅታችንን ከፍተኛ ስልጣን ነው የሚመጻደቁበት። በአገር ላይ በድርጅታችን ላይ በህዝብ ላይ ለፈጸሙት ወንጀል በሁሉም እውነተኛ ታጋዮች ፣በበተኗቸው የትግል ጓዶኞቻችን ጭምር እንዲገመገሙና ጥፋታቸው ተረጋግጦ ለጥፋታቸው ተገቢው ቅጣት እንዲያገኙ ነው የምንጠይቀው።

ፓርቲዬ ከወሰነ ነው የምቆየው የሚሉን፣ በኛ ደምና የመረረ መሰዋትነት በላያችን ላይ የሰበሰቡትን ስብስብ ነው ፓርቲዬ የሚሉት። ወይስ እውነተኛ ታጋዮችን ማለታቸው ነው? ለድርጅቱ ስም ህልውና የምንጨነቀውን አይመስለንም።

ድርጅቱ ከከፈለው መሰዋትነት አኳያ አሸንፈን በደርግ ቦታ ከተቀመጥን በኋላ መለስና ስብስቦቹ ሌት ከቀን ስልጣኑ ላይ የሚቆዩበትን ከጥፋት ላይ ጥፋት የጨመረ መንገድ ባይከተሉ ኖሮ ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ ለድርጅታችን ይህ ሁሉ ጥላቻ አይኖረውም ነበር።

ጥቂት፣ እንደው ጥቂት እንኳ ለፓርቲያችን እዚህ ለመድረስ የተከፈለውን መስዋትነት ቢያስቡ ኖሮ፣ ይህንን ያሰበ ስራ ቢሰሩ ኖሮ፣ ይህ ሁሉ መሰዋትነት የተከፈለበት ድርጅት የህዝብ መሰረት አጥቶ ፓርቲ እንበለው ድርጅት ሆኖ የመቀጠል አደጋ በአልገጠመው ነበር። ብዙዎቻችን እጃችን አለበትና ሆድ ይፍጀው ብለን እንተወው እንጂ በምርጫው እኮ የት እንዳለን አይተንዋል። በእውነቱ ከሆነ የኢህአዲግ አባል ያልሆነ ህዝብን ስራ አትሰራም፤ አትማርም እያለ ማስገደድ ነበረበት። ማነው ለእዚህ ውርደት ህወሃትን ያደረሰው። ትግላችንን፣ መሰዋት የከፈሉ ጓዶቻችንን አደራ በልተን እዚህ ያደረስነው እኛም ነንና ለዚህ ሁላችንም ተጠያቂዎች ነን።

መጨረሻችን ያሳስበን ከጀመረ ቆይቷል።

መስመር እንዳናስይዘው ትክክል አርገን ልንሰራ እንዳንሞክር ሀሳብ እንኳ እንዳናቀርብ አድርገውን ሙሉ መብታችንን ነፍገው፤ ሀይላችንን አሳጥተውናል። ወይ ቦታውን ይዘው አደራቸውን አልተወጡ። ስለስልጣናቸው፡ ስላጋበሱት ገንዘብ ሲሉ ድርጅቱን እዚህ ያደረሱን አቶ መለስና ጥቂት ግብረ-በላዎቻቸው ናቸው።

ይህ በደል ግን ሊያበቃ ይገባዋል። ስለጥፋታቸው የሚገባቸውን ቦታ ሰጥተን፡ የኢትዮጵያ ህዝብ መሰዋእትነታችንን ከጥፋታችን ማመዛዘን የሚችል ነውና ይቅርታ ጠይቀንም ቢሆን ብዙ የትግል ጓዶቻችንን ዘመዶቻችንን ያጣንበትን ድርጅት ህይወት ያለው ቀጣይነት ያለው ማድረግ ነው ያለብን ማድረግም የምንፈልገውም።

እነመለስና ስብስባቸው ሁሉም በቂ ገንዘብ እንደዘረፉ አውቀናል። ሁሉም በውጪ ቤት ገዝተዋል። ሁሉም ፓስፖርት አላቸው። ሁሉም ልጆቻቸውን ወደውጪ ቀድመው ልከዋል። በደንብ አስተምረዋል። ለራሳቸው ለነጋቸው አንዴም ማሰብ ያቆሙበት ጊዜ የለም። መስኗቸው ነው እንጂ ሞተናላ።

ተክላይና ጓዶቹ

### ከግንቦት 7 ድምጽ የዝግጅት ክፍል የተሰጠ አስተያየት

ውድ አቶ ተክላይ፡ እርስዎና ጉዋዶችዎ ለላኩልን ጽሁፍ እናመሰግናለን።አሳብ አይግባዎት። ሀቅን ይዞ የሚመጣ ጽሁፍ እስከሆነ ከማንም ቢመጣ እናስተናግዳለን፡ንቅናቄያችን ሁሌም ቢሆን የለየላቸውን ጸረ-ኢትዮጵያ የሆኑትን መለስንና በጣት የሚቆጠሩ ባለደረቦቹን እንጂ የወያኔን አባላት በሙሉ በአንድ ቀለምና ብሩሽ ቀብቶ አይቷቸው አያውቅም። እውነት ብለዋል። እኛም መክረናል። የነመለስ ጥፋት ብዙ ነው፤ በሃገርና በህዝብ ላይ የፈጸሙት ወንጀል ግዙፍ ነው። ህዝብ ይህን የእነመለስን ወንጀል ከኢህአዴግ ለይቶ ለማየት እንዲችል ለማድረግ ቀላል አይደለም። ግን እርስዎና ጓዶችዎ እንደሚሉት ከበረታችሁ አሁንም መፍትሄ ይኖረዋል። እኛም እናንተን ለማገዝ አንቸገርም።

### ማረሚያ

በላፈው ሳምንት የኢትዮጵያው መንግስት ሰራተኛ፡ዋና ግፍ ቀማሽ እና ታላቅ የለውጥ ሃይል በሚል ርእስ ያቀረብነው መጣጥፍ የተጻፈው በታሪኬ ለማ መሆኑን እየገለጽን በተስፋዬ ማሩ በማለት ለሰራነው ስህተት ተስፋዬ ማሩንና አንባቢን ይቅርታ እንጠይቃለን።




# Monday 2nd March 2009

በሐገራችን ውያኔ / ኢሕአደግ በሕዝብ ላይ እያደረሰ ያለውን ከፍተኛ የመብት እረገጣ፣ አፈና እና ሐገር መሸጥ፣ ለመቃወም እና በግፍ በእሥር እየማቀቁ ያሉትን፡-

- ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ፣ በሐገራችን የመጀመሪያዋ የትልቅ የፖለቲካ ድርጅት ፣አንደነት ለዴሞክራሲ እና ፍትህ ፓርቲ ፣ የሴት መሪ፣
  ለፍትህ ለዴሞክራሲና ለሰብዓዊ መብት ባላት ከፍተኛ ተቆርቋሪነት ለእድሜ ልክ እሥር የተዳረገች፣
- ቴዲ አፍሮ፣ ስለ ሰላም ፍቅርና አንድነት ባለው የተለየ የአርትስትነት ችሎታ ማስተማሩ ወንጀል ሁኖ ለእሥር የተዳረገ ወጣት፣
- በሰበብ አስባቡ ለከፍተኛ መንገላታትና እስር የተዳረጉ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወገኖቻችን፣ በአስቸኳይ እንዲፈቱ ለመጠይቅ፣ እና
- ወያኔ የሐገራችንን ከፍተኛ መሬት ለፖለቲካ ጊዚያዊ ጥቅም፣ ለሱዳን በመሸጡ የተሰማንን ቁጣ ለመግለጽ፣

በመጭው ማርች 2 ቀን 2009 ዓ.ም በመላው አለም ከፈተኛ የተቃውሞ ሰልፍ ተዝጋጂቷል ፣ ለፍትህ ፣ ለሰበዓዊ መብት ለሐገር ህልውና የቆማችሁ ወገኖ በሙሉ፣ ጊዜው አሁን ነውና በዚህ ሰልፍ ተገኝታችሁ ድምጻችሁን እንድታሰሙ ወገናዊ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

**USA: Protest March from States Department to the White House**
2200 C S1 NW, Washington DC, USA.
Starting from 9:00am

**UK: Embassy of The United States**
24 Grosvenor Square, London W1A 1AE
from 3pm to 7pm, Info: 07946644831, 07970350860

**Norway: Embassy of The United States**
Henrik Ibsens gate 85, Oslo, Norway
From 13:00 to 16:00. Info: 047 41560745.

**Switzerland: Embassy of The United States**
Sulgeneckstrasse 19, CH-3007 Berne, Switzerland
Info: 041448110806, 041223410013

**Italy: Embassy of The United States**
VIA VITTORIO VENETO, Roma, Italy
from 15:00 - 18:00

**Germany: United States Consulate**
Königsstrasse, Munich, Germany
starting from 13:00pm

**Sweden: Embassy of The United States**
Dag Hammarskjölds Vägen 31, 115 89 STOCKHOLM
from 13:00-16:00 Info: 046-73 657 0916

**Australia: United States Consulate**
553 St Kilda Road, Melbourne, Australia 3004
from 11.00am Info: 0411895564

አለም አቀፍ ለፍትህና ሰበአዊ መብት በኢትዮጵያ አሰተባባሪ ኮሚቴ፣